# የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሲፒርየር ፍርድ ቤት

# በዋና ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) ጀሰ-ሀሪንግ የተላለፈ ትዕዛዝ

# (12/30/21)

የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሲፒርየር ፍርድ ቤት ለጁሪ ግዴታ (ጁሪ ዲዩቲ) ለሚመጡ፣ ለተከራካሪ ወገኖች፣ ለምስክሮች፣ ለጠበቆች፣ ለፍርድ ቤት ሰራተኞች፣ እና ለማናቸውም ሌላ በፍርድ ቤት ያለ ሰው ጤናና ደህንነት የመጠበቅ ሀላፊነት አለበት፣ ስለዚህም ከማህበረሰብ ጤና ባለሞያዎች ጋር በመመካከር በቀጣይነት በአለማችን ያለውን አለም አቀፋ ወረርሽን ይከታተላል። በቅርቡ የታየው የኮሮና ቫይረስ መጨመር እንደሚቀጥል ትንበያ ያለ በመሆኑ ምክኒያት ፍርድ ቤቱ ጊዜያዊ የአሰራር ማሻሻያዎች እንዲያደርግ ተገዷል። ይህ ትእዛዝ በኖቨምበር 21፣ 2021 የተላለፈውን የዋና ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) ትእዛዝን ያሻሽላል። በዚህ ትእዛዝ ከተሻሻለው በስተቀር የኖቨምበር 21፣ 2021 ትእዛዝ በሙሉ ሃይልና ውጤት ተፈጻሚ ይሆናል።

## <u>የፍትሐ ብሔር ክፍል (ሲቪል ዲቪዥን)</u>

እስከ ጁላይ 11፣ 2022 የተቀጠሩ በጁሪ የሚዳኙ ክርክሮች (ጁሪ ትራያልስ) ከፌብርዋሪ 11፣ 2022 በኋላ ባሉ በተቻለ መጠን በቀረበ ቀን ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጣቸዋል።

## <u>የወንጀለኛ  ክፍል (ክሪሚናል ዲቪዥን)</u>

የወንጀለኛ ክፍል እንደሚከተለው ይሰራል፡

እስከ ፌብርዋሪ 10፣ 2022 ተቀጥረው ያሉ በጁሪ የሚዳኙ ክርክሮች (ጁሪ ትራያልስ) ከፌብርዋሪ 11፣ 2022 በኋላ ባሉ በተቻለ መጠን በቀረበ ቀን ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጣቸዋል። ማናቸውም ተጀምረው ያሉ በጁሪ የሚዳኙ ክርክሮች (ጁሪ ትራያልስ) በተቻለ መጠን በፍጥነት ይጠናቀቃሉ። የቅድሚያ ችሎቶች (ፕረሊሚናሪ ሂሪንግስ)፣ የእስር ችሎቶች (ዲቴንሽን ሂሪንግስ)፣ እና በጁሪ የማይዳኙ ክርክሮች (ናን-ጁሪ ትራያልስ) ተሰጥቷቸው ባለ ቀጠሮ ይቀጥላሉ።

ተጨማሪ ማስታወቂያ እስኪሰጥ ድረስ የሚከተሉት ቀጠሮዎች ሙሉ በሙሉ በርቀት የሚከናወኑ ሲሆን ሁሉም ተከራካሪ ወገኖች በተቻላቸው መጠን በቪድዮ መቅረብ ይኖርባቸዋል፣ በቪድዮ መቅረብ የማይችሉ ከሆነ ግን በቴሌፎን መቅረብ ይችላሉ። በርቀት ችሎት መቅረብ የማይችሉ ግለሰቦች በማህበረሰቡ ያሉትን በርቀት ችሎት ለመከታተል የሚያስችሉ ቦታዎች (ኮሚኒቲ ሳይትስ) ለመጠቀም ወደ 202-879-1900 ወይም ወደ DCCourtsRemoteSites@dcsc.gov ኢ-መይል መላክ ይችላሉ። የማህበረሰብ ቦታዎች (ኮሚኒቲ ሳይትስ) በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ይህንን

www.dccourts.gov/sites/default/files/Remote-Hearing-Sites-Tip-Sheet-3.pdf
ይመልከቱ።

- ዩ.ኤስ.ኤ./ኦ.ኤ.ጂ. የጥቅስ የእምነት ክህደት እና አቅጣጫ መቀየርያ ካላንደር (ሳይቴሽን አረይንመንት ኤንድ ዳይቨርዥን ካላንደር)
- የአእምሮ ጤና የማህበረሰብ ፍርድ ቤት
- የሱፒርየር ፍርድ ቤት የአደንዛዥ እጽ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራም (የአደንዛዥ እጽ ፍርድ ቤት)

- የእምነት ክህደት ችሎቶች (አረይንመንትስ) እና መቅረቦች (ፕረዘንትመንትስ) በፍርድ ቤት ክፍል ቁጥር C-10 ይሰማሉ። እስከ ፌብርዋሪ 12፣ 2022 ድረስ፣ የሚያዋጣ እስከሆነ ድረስ፣ እስር ቤት እንዲቆዩ የተጠየቀባቸው አዳዲስ ቁጥጥር ስር ውስጥ የገቡ ተከላካዮች ወደ C-10 እንዲመጡ ይደረጋል፣ የተቀሩት ተከላካዮች በርቀት ይቀርባሉ። ተረኛ የተከላካይ ጠበቃ (ስታንድ-ኢን ዲፌንስ ካውንስል) እና በC-10 የተመደቡ አቃቤ ህጎች በአካል መቅረብ ይኖርባቸዋል፣ የተቀሩት በልዩ ሁኔታ የተመደቡ የመንግስትና የተከላካይ ጠበቆች በርቀት እንዲቀርቡ ይበረታታሉ። በዲ.ሲ. እስር ቤት (ጀይል) ታስረው ያሉ ተከላካዮች በቪድዮ መቅረቡን ይቀጥላሉ። የወደ ሌላ ክልል የሸሸ ወንጀለኛ መዝገቦች (ፉጂቲቭ ማተርስ) ተከላካዮች ወደ ተከሰሱበት እንዲሄዱ የሚደረጉ ችሎቶች (ኤክስትራዲሽን ሂሪንግስ) እስከ ፌብርዋሪ 9፣ 2022 ድረስ C-10 መሰማት ይቀጥላሉ፣ እና ከፌብርዋሪ 16፣ 2022 ጀምሮ ያሉ ተከላካዮች ወደ ተከሰሱበት እንዲሄዱ የሚደረጉ ችሎቶች (ኤክስትራዲሽን ሂሪንግስ) በዋና ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) ይቀጠራሉ።

- ከፌብርዋሪ 12፣ 2022 በኋላ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ አይደለም በሚል ውሳኔ ላይ ካልተደረሰ በስተቀር፣ የመንግስትና የተከላካይ ጠበቆች እና ተከላካዩ፣ በቪድዮ መቅረብ የሚቀጥሉትን በዲሲ እስር ቤት (ዲ.ሲ. ጀይል) ታስረው ካሉ ተከላካዮች በስተቀር፣ በፍርድ ቤቱ በአካል ይቀርባሉ።

- ሁሉም በእስር-የሌሉና በእስር ያሉ መዝገቦች በተመደበው የቀላል ወንጀል የማህበረሰብ ፍርድ ቤት (ሚስደሚነር ኮሚዩኒቲ ኮርት) እና በከባድ ወንጀል ካላንደሮች (ፌለኒ ካላንደርስ) በተመደበላቸው የፍርድ ቤት ክፍል በርቀትና በአካል መከናወኑ ይቀጥላሉ። የቀላል ወንጀል የማህበረሰብ ፍርድ ቤት (ሚስደሚነር ኮሚዩኒቲ ኮርት) ካላንደሮች በአርብ እለት በርቀት ይከናወናሉ (ይህ የማይሆነው በሲንየር ዳኛ ካላንደር ያሉ ከሆነ በጁሪ የማይዳኝ ክርክር (ናን-ጁሪ ትራያል) መጠናቀቅ ይኖርበታል)።

- ሁሉም የፍርድ ቤት ክፍሎች፣ የተከላካዮች፣ ምስክሮች፣ ተበዳዮች፣ ጠበቆች፣ የፍርድ ቤት ሰራተኞች፣ ጁረሮች እና ሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ጤናና ደህንነት በሚጠብቅ መልክ በአካልና በርቀት ለማሳተፍ ተዋቅረዋል።

- **ከእስር ተፈተው ያሉ ተከላካዮች** እስከተቻለ ድረስ በቪድዮ መቅረብ ይችላሉ፣ በቪድዮ መቅረብ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ፣ ፍርድ ቤቱ በአካል እንዲቀርቡ ካላዘዘ በስተቀር፣ በቴሌፎን መቅረብ ይችላሉ።
- ለክርክር (ትራያል)፣ እና እስር እና ቅድሚያ ችሎቶች (ዲተንሽን ኤንድ ፕረሊሚናሪ ሂሪንግስ) በስተቀር፣ **በዲፓርትመንት ኦፍ ሪሃብሊቴሽን ሰርቪስስ (በተሀድሶ አገልግሎቶች ክፍል)፣ በእስር ቤቶች ቢሮ (ቢሮ ኦፍ ፕሪዝንስ)፣ እና በዲፓርትመንት ኦፍ ቢሄቭየራል ሄልዝ (የባህርይ ጤና ክፍል) ስር ያሉ ተከላካዮች በርቀት መቅረቡን መቀጠል ይችላሉ።**
- ለክርክር (ትራያል)፣ እና እስር እና ቅድሚያ ችሎቶች (ዲተንሽን ኤንድ ፕረሊሚናሪ ሂሪንግስ) በስተቀር፣ **በዲፓርትመንት ኦፍ ኮሬክሽንስ (በማረሚያ ቤት ክፍል) ስር በቀላል ወንጀል መዝገቦች ያሉ ተከላካዮች በርቀት መቅረቡን መቀጠል ይችላሉ።**
- ተከላካይ በችሎት የመቅረብ መብቱን በገዛ ፈቃዱ እተዋለሁ ካላለ፣ ወይም በህክምና እንዲቀርብ ያማይፈቀድለት ከሆነ በስተቀር **በዲፓርትመንት ኦፍ ኮሬክሽንስ (በማረሚያ ቤት ክፍል) ስር በከባድ ወንጀል መዝገቦች ያሉ ተከላካዮች በአካል ይቀርባሉ።**
- እስከ ፌብርዋሪ 11፣ 2022 ድረስ **ሁሉም የተከላካይ ጠበቆችና ሁሉም በልዩ ሁኔታ የተመደቡ አቃቤ ህጎች** ጉዳዩ የመጀመሪያ ችሎት (ፕረሊሚናሪ ሂሪንግ)፣ የእስር ችሎት (ዲቴንሽን ሂሪንግ)፣ ክርክር (ትራያል)፣ ወይም ሌላ ማስረጃ የሚሰማበት ችሎት ካልሆነ በስተቀር በሁሉም ችሎቶች በርቀት መቅረብ ይችላሉ።
- እስከ ፌብርዋሪ 11፣ 2022 ድረስ፣ በርቀት ለመቅረብ ጥያቄ ማቅረብ የሚፈልግ **ማናቸውም በካላንደር-የተመደበ አቃቤ ህግ** በርቀት መቅረቡ ለምን እየተጠየቀ እንዳለ ምክንያት ለማቅረብ፣ ውሳኔው የያንዳንዱን ሁኔታ በመመልከት በዳኛው የሚወሰን ይሆናል፣ የዳኛው ጽህፈት ቤት (ቻምበርስ) ማግኘት ያስፈልጋል።
- ከፌብርዋሪ 11፣ 2022 በኋላ፣ ተከላካዩ በርቀት የሚቀርብ ከሆነ፣ **የመንግስት እና የተከላካይ ጠበቆች** በቪድዮ መቅረብ ይኖርባቸዋል።
- ከፌብርዋሪ 11፣ 2022 በኋላ፣ ተከላካዩ በአካል የሚቀርብ ከሆነ፣ **የመንግስት እና የተከላካይ ጠበቆች** በአካል መቅረብ ይኖርባቸዋል።
- በግለሰብ መዝገብ በርቀት ምስክርነት እንዲሰጡ ፍርድ ቤቱ ካልፈቀደ በስተቀር በሁሉም ሂደቶች ያሉ **ምስክሮች** መቅረብ ይኖርባቸዋል።
- **የቅድመ ክርክር አገልግሎቶች (ፕሪትራያል ሰርቪስስ) እና የፍርድ ቤት አገልግሎቶች እና የበዳይ ክትትል ኤጀንሲ ተወካዮች** በአካል መሳተፍ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከተቻለ በርቀት በቪድዮ፣ በቪድዮ መቅረብ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ በቴሌፎን እንዲቀርቡ ይበረታታሉ።
- **የወንጀል ሰለባዎች** በአካል መሳተፍ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከተቻለ በርቀት በቪድዮ ወይም በቴሌፎን እንዲቀርቡ ይበረታታሉ።

- ○ የአቅም ገደቦች ታሳቢ ባደረገ መልኩ **የማህበረሰቡ አባላት** በአካል መሳተፍ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከተቻለ በርቀት በቪድዮ ወይም በቴሌፎን እንዲቀርቡ ይበረታታሉ።

**<u>የቤት ውስጥ ሁከት ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን)</u>**

በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር በአስቸኳይ ጊዜ መፈጸም የነበረባቸው በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸው እና በሌሎች ትዕዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜ በስራ ላይ እስካለ ድረስ፣ ተጨማሪ ትዕዛዝ እስኪሰጥ ድረስ፣ ይታገዳሉ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ ይራዘማሉም።

የቤት ውስጥ ሁከት ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን) (ዲ.ቪ.ዲ.) እንደሚከተለው ይሰራል፡

- የቤት ውስጥ ሁከት ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን) የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በአካልና በርቀት ከ8:30 ኤ.ኤም. እስከ 5፡00 ፒ.ኤም. ድረስ ከሰኞ እስከ አርብ ድረስ ይገኛል።

- የማህበረሰቡና የሰራተኞቹ ጤናና ደህንነት ለመጠበቅ የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) ማህበራዊ ርቀት እና የብዛት ገደቦች ይጠቀማል። የተወሰኑ ሰራተኞች በአካል በፍርድ ቤቱ የሚሰሩ ሲሆን ሌሎች ሰራተኞች በርቀት መስራቱን ይቀጥላሉ።

- የፍትሐብሔር ፋይል የሚደረጉ ነገሮች በጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በአካል ወይም በርቀት መደረግ ይችላሉ፡
    1. በበይነ መረብ (ኦንላይን) በwww.probono.net/dccourts፣ ወይም፣
    2. በዲ.ቪ.ዲ. ድረገጽ የሚገኙትን ቅጾች ሞልቶ ወደ DVD@dcsc.gov ኢመይል በማድረግ። ሊሞሉ የሚችሉ ቅጾች ለማግኘት በሚከተለው ይጫኑ፡ here (ከዚህ)።

- በዲ.ቪ.ኤም. እና በሲ.ሲ.ሲ. መዝገቦች የወንጀለኛ ፋይል የሚደረጉ ነገሮች ኬዝፋይልኤክስፕረስ በመጠቀም በበይነ መረብ (ኦንላይን) ፋይል ማድረጉ መቀጠል ይኖርባቸዋል።

- አብዛኛዎቹ ዳኞችና የፍርድ ቤት ሰራተኞች በርቀት መስራት ይቀጥላሉ። ተከራካሪ ወገኖች፣ በከፊል በርቀት በሚካሄድ ፍርድ ቤት በአካል እንዲቀርቡ በልዩ ሁኔታ ካልታዘዙ በስተቀር፣ በዲ.ቪ.ዲ. የርቀት ፍርድ ቤቶች (ሪሞት ኮርትሩምስ) በቴሌፎን ወይም ቪድዮኮንፈረንስ መቅረብ መቀጠል ይችላሉ።

- በዲ.ቪ.ዲ. የሚካሄዱ የፍርድ ቤት ሂደቶች ለህዝብ ክፍት ናቸው። ተከራካሪ ወገኖች ወደ ፍርድ ቤት ክፍሉ እንዴት በቀጥታ መግባት እንደሚችሉ መመርያዎች ያገኛሉ። ተከራካሪ ወገኖች-ያልሆኑ የዲ.ቪ. ክፍል የጸሀፊ ቢሮን በ (202) 879-0157 በመደወል ወይም ወደ DVDhearings@dcsc.gov ኢመይል በማድረግ ወደሚፈልጉት ፍርድ ቤት ክፍል መግቢያ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

- ስድስት የፍርድ ቤት ክፍሎች በርቀት (ሪሞትሊ) ወይም በከፊል በርቀት (ፓርሻሊ ሪሞትሊ)፣ ፍርድ ቤቱ ያዘዘ ከሆነ ደግሞ በአካል፣ እየሰሩ ይገኛሉ። እባክዎን ከታች ያሉትን የፍርድ ቤት ክፍሎች ዝርዝር በፍርድ ቤቱ ከተመደቡ የችሎቶች አይነቶች ጋር ይመልከቱ፡

    - 113 – የሲ.ፒ.ኦ.፣ ኤ.ኤስ.ኦ.፣ ኢ.አር.ፒ.ኦ. መዝገቦች
    - 114 – የሲ.ፒ.ኦ.፣ ኤ.ኤስ.ኦ.፣ ኢ.አር.ፒ.ኦ. መዝገቦች
    - 117 – የዲ.ቪ.ኤም.፣ ሲ.ሲ.ሲ. እና ኢ.አር.ፒ.ኦ. መዝገቦች
    - 118 – የዲ.ቪ.ኤም.፣ ሲ.ሲ.ሲ. እና ኢ.አር.ፒ.ኦ. መዝገቦች
    - 119 –የቲ.ፒ.ኦ.፣ ቲ.ኤ.ኤስ.ኦ. እና የልጅ ቀለብ ጉዳዮች
    - JM-9 – ተጠባባቂ የቲ.ፒ.ኦ.፣ ቲ.ኤ.ኤስ.ኦ.

<u>የወንጀለኛ መዝገቦች – የቤት ውስጥ ሁከት ቀላል-ወንጀል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ሚስደሚነር) (ዲ.ቪ.ኤም.) እና የፍርድ ቤት መድፈር ወንጀል (ክሪሚናል ኮንተምፕት) (ሲ.ሲ.ሲ.)</u>

- ሁሉም በፍርድ ቤት ክፍል ቁጥር 117 እና በፍርድ ቤት ክፍል ቁጥር 118 የተቀጠሩ የከእስር የተፈቱ ተከላካዮች በአካል የሚካሄዱ ክርክሮች **<u>ወደ በርቀት የሚካሄዱ ጉዳዩ ያለበት ደረጃ የሚታወቅበት ችሎት (ስታተስ ሂሪንግ) ይቀየራሉ</u>**። በርቀት የሚደረግ ችሎት የሚፈልጉ ከሆነ ጠበቆች የተመደበውን ዳኛ ማግኘት ይኖርባቸዋል። ጉዳዩ ያለበት ደረጃ በሚታወቅበት ችሎት (ስታተስ ሂሪንግ) ጊዜ አዲስ የክርክር ቀናት ይመደባሉ።

- <u>በተቀጠሩት ችሎቶች መቅረብ፡</u> የዲ.ቪ. ክፍል የወንጀለኛ የፍርድ ቤት ክፍሎች በርቀት መስራቱ ይቀጥላሉ። በርቀት የሚካሄዱ ችሎቶች ተከላካዮች ከዲ.ሲ. እስር ቤት (ጀይል) ወይም ከማህበረሰቡ (ኮሚኒቲ) እየቀረቡ በቴሌፎን ወይም በቪድዮኮንፈረንስ ይካሄዳሉ። ጠበቃ፣ የቅድመ-ክርክር አገልግሎቶች ተወካዮች፣ እና የፕሮቤሽን ኦፊሰሮች በቪድዮ ወይም ቴሌፎን በመጠቀም በርቀት መቅረብ ይችላሉ። ምስክሮች በያንዳንዱ መዝገብ በፍርድ ቤቱ እስከተፈቀደ ድረስ ቪድዮ ወይም ቴሌፎን በመጠቀም በርቀት መቅረብ ይችላሉ።

- <u>የበእስር ያሉ ማስረጃ-የሚሰማባቸው ችሎቶች (ዲተይንድ ሳብስታንቲቭ ሂሪንግስ)</u>፡ ተከላካዩ በዲ.ቪ.ኤም. ወይም ሲ.ሲ.ሲ. መዝገቦች የታሰረ የእስር ችሎቶች (ዲቴንሽን ሂሪንግስ) ወይም ሌላ ማስረጃ-የማይሰማባቸው ችሎቶች በሀሙስ እለት በርቀት በሚካሄድ የዲ.ቪ.ዲ. ፍርድ ቤት ክፍል ይካሄዳል። ተከላካዮች ከዲ.ሲ. እስር ቤት (ዲ.ሲ. ጀይል) በቪድዮ ወይም ቴሌፎን ይቀርባሉ።

- <u>በእስር ያሉ ተከላካዮች (ዲተይንስ ደፈንዳንትስ)</u>፡ የእምነት ክህደት ቃላቸው ከሰጡ በኋላ በ C-10 የታሰሩ ተከላካዮች በ C-10 ችሎት ከቀረቡ ከአንድ ሳምንት በኋላ ጉዳዩ ያለበት ደረጃ የሚታወቅበት በርቀት የሚካሄድ ችሎት (ሪሞት ስታተስ ሂሪንግ) ቀጠሮ ይሰጣቸዋል። መዝገቦቹ በተመደበው ዳኛ ጉዳዩ ያለበት ደረጃ የሚታወቅበት ችሎት (ስታተስ ሂሪንግ) ካላንደር ቀጠሮ ይያዝላቸዋል። የተከላካይ ጠበቃና አቃቤ ህግ ለችሎቱ በአካል መቅረብ ይኖርባቸዋል። በዚህ ችሎት ተከራካሪ ወገኖች የእስር ችሎት (ዲቴንሽን ሂሪንግ) ወይም ተጨማሪ ጉዳዩ ያለበት ደረጃ የሚታወቅበት ቀጠሮ መጠየቅ ይችላሉ።

- <u>የእስር ችሎቶች (ዲቴንሽን ሂሪንግስ)</u>፡ የመጀመሪያ ጉዳዩ ያለበት ደረጃ የሚታወቅበት ችሎት (ስታተስ ሂሪንግ) ከተደረገ በኋላና ጥያቄ ከቀረበ የዲ.ቪ. የእስር ችሎቶች በአካል ይካሄዳሉ። ሁሉም አካላት በነዚህ ችሎቶች በአካል መገኘት ይኖርባቸዋል። እነዚህ ችሎቶች በተመደበው ማጂስትሬት ዳኛ ይሰማሉ።

- <u>በእስር-ያሉ በጁሪ-የማይዳኙ ክርክሮች (ዲተይንድ ናን-ጁሪ ትራያልስ)</u>፡ ዲ.ቪ.ዲ. ከዲሰምበር 2፣ 2020 ጀምሮ በእስር-ያሉ በጁሪ-የማይዳኙ ክርክሮች (ዲተይንድ ናን-ጁሪ ትራያልስ) መስማት ለመቀጠል የ30-ቀን ማስታወቂያ በኖቨምበር 2፣ 2020 አቅርቦ ነበር። በእስር-ያሉ በጁሪ-የማይዳኙ ክርክሮች (ዲተይንድ ናን-ጁሪ ትራያልስ) ፍርድ ቤቱ በሚይዘው ጉዳዩ ያለበት ደረጃ በሚታወቅበት ችሎት ቀጠሮ ይያዝላቸዋል።

- <u>የእምነት ክህደት ቃሎች (አረይንመንትስ)</u>፡ የቤት ውስጥ ሁከት የእምነት ክህደት ችሎቶች (አረይንመንትስ)  በፍርድ ቤት ቁጥር C-10 መሰማት ይቀጥላሉ። የሲ.ሲ.ሲ. የእምነት ክህደት ችሎቶች (አረይንመንትስ) በርቀት በሚካሄድ የዲ.ቪ.ዲ. የፍርድ ቤት ክፍል ይሰማሉ።

- <u>ምክኒያት አሳይ ችሎቶች (ሾው ከውዝ ሂሪንግስ)</u>፡
    - በከፊል በርቀት የሚካሄዱ የቅድመ-ክርክርና የብሮቤሽን ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ) ችሎቶች በዲ.ቪ.ዲ. የፍርድ ቤት ክፍል በሰኞና እሮብ እለታት ይካሄዳሉ። ተቀባይነት ያለው የኮቪድ-19 ፕሮቶኮል ካለፉ በኋላ ተከላካዮች ዳኛው ፊት በአካል ይቀርባሉ። ሁሉም ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች በቴሌፎን ወይም በቪድዮኮንፈረንስ መቅረብ ይችላሉ።

- ሙሉ በሙሉ በርቀት የሚካሄዱ የቅድመ-ክርክርና የብሮቤሽን ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ) ችሎቶች በማንኛውም ቀን፣ ከሰኞ እስከ አርብ ሊቀጠሩ ይችላሉ። ተከላካዮች ጨምሮ ሁሉም ተከራካሪ ወገኖች በቴሌፎን ወይም በቪድዮኮንፈረንስ በርቀት መቅረብ ይኖርባቸዋል።
- በጃንዋሪ 1፣ 2022 ወይም ከዚህ ቀን በኋላ የተቀጠሩ የፕሮቤሽም ምክኒያት አሳይ ችሎቶች (ፕሮቤሽን ሾው ከውዝ ሂሪንግስ) ፍርድ ቤቱ ካላዘዘ በስተቀር በተቀጠረው ቀን በርቀት በሚካሄድ የፍርድ ቤት ክፍል ይካሄዳሉ። ኤ.ቪ.አር. ፋይል ማድረግ የፕሮቤሽኑ ማብቅያ ጊዜ ያቆመዋል (ቶል ያደርገዋል)።

- ፍርድ ቤት ሲመጡ በፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ እንዲታሰሩ የሚፈቅድ ማዘዣ (ዋክ-ኢን ቤንጅ ዋራንት) መዝገቦች፡ የፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ የወጣላቸው ተከላካዮች **በሰኞ** ከሰአት በፍርድ ቤት ክፍል ቁጥር 118፣ **በአርብ** ከሰአት በፍርድ ቤት ክፍል ቁጥር 118፣ በሌሎች ቀናት ደግሞ በተመደቡ ፍርድ ቤቶች ራሳቸውን እጅ መስጠት ይችላሉ። **በማክሰኞ፣ ሐሙስ እና አርብ** የፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ የወጣላቸው ተከላካዮች ወደሚከተሉት የፍርድ ቤት ክፍሎች ራሳቸውን እጅ መስጠት ይችላሉ፡
  - ጃንዋሪ 3-14፣ 2022- ፍርድ ቤት ክፍል ቁጥር 303
  - ጃንዋሪ 18-28፣ 2022- ፍርድ ቤት ክፍል ቁጥር 201

  የፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ የወጣላቸው ተከላካዮች በተጨማሪ ከ3:30 ፒ.ኤም. በፊት ለዲ.ቪ.ዲ. የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክስ ኦፊስ) ራሳቸውን እጅ መስጠት ይችላሉ፣ የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክስ ኦፊስ) በበኩሉ በቀኑ በተመደበው ዳኛ ፊት ወይም በተመደበው ፍርድ ቤት ክፍል ችሎት እንዲቀርቡ ያደርጋል።

<u>የፍትሐብሔር መከላከያ ትዕዛዝ (ሲቪል ፕሮቴክሽን ኦርደር) (ሲ.ፒ.ኦ.ስ) መዝገቦች፣ የጸረ-ማሳደድ ትዕዛዝ (አንታይ-ስቶኪንግ ኦርደር) መዝገቦች፣ እና ከፍተኛ አደጋ መከላከያ ትዕዛዞች (ኤክስትሪም ሪስክ ፕሮቴክሽን ኦርደርስ) (ኢ.አር.ፒ.ኦ.ስ) መዝገቦች፡</u> የቤት ውስጥ ሁከት ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን)፣ በርቀት የሚካሄዱ ችሎቶች ለማቀላጠፍ ሁሉንም ተከራካሪ ወገኖች ሊገኙባቸው የሚችሉ እንደነ የቴሌፎን ቁጥሮችና ኢመይል አድራሻዎች የመሳሰሉ የመገኛ መረጃዎች ለመስጠት ጸሀፊ ቢሮን (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በቴሌፎን ቁጥር (202) 879-0157 ያገኙ ዘንድ ያበረታታል። እባክዎ፣ የገዛ ራስዎትን ወይም የተቃራኒ አካልን የመገኛ መረጃ ለመስጠት ወደዚህ የቴሌፎን ቁጥር ይደውሉ።

<u>የፍትሐብሔር መከላከያ ትዕዛዝ (ሲቪል ፕሮቴክሽን ኦርደር) (ሲ.ፒ.ኦ.ስ) ጥያቄዎች</u>፡

- የቲ.ፒ.ኦ. ጥያቄዎች መዝገቦች በርቀት በሚሰማ ዳኛ (ሪሞት ጃጅ) ይሰማሉ። ከጃንዋሪ 3፣ 2022 ጀምሮ የተደረጉ አዳዲስ የቲ.ፒ.ኦ. ጥያቄዎች ፋይል ከተደረገ በኋላ ባሉ 2 ወይም 3 ሳምንታት አገልግሎታቸው ያበቃል።

- ተከራካሪ ወገኖች ቲ.ፒ.ኦ. እና ሌሎች ከጉዳዩ ተያያዥነት ያላቸው ወረቀቶች (እንደነ በሰው በኩል የፍርድ ቤት መጥሪያ ማድረሻ ሰነዶች)፣ በኢመይል ጭምር፣ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ይደርሳቸዋል። በአካል ፋይል አድራጊዎች፣ ፋይል ያደረጉዋቸውን ወረቀቶች ቅጂ በወረቀት እንዲሰጣቸው ከጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) መጠየቅ ይችላሉ።

- ሁሉም የሲ.ፒ.ኦ እና ተመሳሳይ መዝገቦች ጉዳዩ ፋይል ከተደረገ በኋላ ከሁለት ሳምንታት አከባቢ ይካሄዳሉ። በተጨማሪ፣ ተከራካሪ ወገኖቹ ከጠየቁና ፍርድ ቤቱም ክፍት ቦታ ካለው፣ ተከራካሪ ወገኖች የሲ.ፒ.ኦ. እና ኤ.ኤስ.ኦ. ጉዳያቸው ከተመደበው ቀን የቀረበ የችሎት ቀን እንዲሰጣቸው መጠየቅ ይችላሉ።

<u>አንድ አካል ብቻ ባለበት የተወሰኑ የሲ.ፒ.ኦ. መዝገቦች (ዲፎልት ሲ.ፒ.ኦ. ኬዝስ) የፍርድ ቤት የእስር ማዘዣዎች (ቤንች ዋራንትስ)፡</u> የፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ የወጣላቸው መልስ ሰጭዎች (ሪስፖንደንትስ) በዛኑ ቀን በአካል ዳኛ ፊት ይቀርቡ ዘንድ በዲ.ቪ.ዲ. የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በ3:30 ፒ.ኤም. ራሳቸውን እጅ መስጠት ይችላሉ። ወይም የጸሀፊ ቢሮን በ (202-879-0157) በማግኘት የፍርድ ቤት የእስር ትእዛዝ በተመለከተ ለመነጋገር በርቀት የሚካሄድ ችሎት ቀጠሮ ማስያዝ ይችላሉ።

<u>በሲ.ፒ.ኦ. ምክኒያት የተነሱ የልጅ ቀለብ (ቻይልድ ሳፖርት) መዝገቦች</u>

- የቤት ውስጥ ሁከት ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን) ወደ ክፍሉ የተመደቡ የልጅ ቀለብ መዝገቦች በምናባዊ የፍርድ ቤት ክፍል (ቨርቹዋል ኮርትሩም) ይሰማል። ተከራካሪ ወገኖች ከተመደበው ቀነ ቀጠሮ በፊት ምናባዊው ችሎት (ቨርቹዋል ሂሪንግ) እንዴት መቀላቀል እንደሚቻል የሚያሳዩ ማስታወቂያና መመሪያዎች ያገኛሉ።

<u>የጸረ-ማሳደድ ትዕዛዝ (አንታይ-ስቶኪንግ ኦርደር) መዝገቦች (ኤ.ኤስ.ኦ.ስ) ጥያቄዎች፡</u>

- ጊዜያዊ የጸረ-ማሳደድ ትዕዛዝ (አንታይ-ስቶኪንግ ኦርደር) ጥያቄዎች መዝገቦች በርቀት በሚሰማ ዳኛ (ሪሞት ጃጅ)። ከጃንዋሪ 3፣ 2022 ጀምሮ የተደረጉ አዳዲስ የቲ.ኤ.ኤስ.ኦ. ጥያቄዎች ፋይል ከተደረገ በኋላ ባሉ 2 ወይም 3 ሳምንታት አገልግሎታቸው ያበቃል።

- ተከራካሪ ወገኖች ቲ.ፒ.ኦ. እና ሌሎች ከጉዳዩ ተያያዥነት ያላቸው ወረቀቶች (እንደነበራስ መንገድ ሰነዶቹን ለተከላካይ ማድረሻ ሰነዶች)፣ በኢመይል ጭምር፣ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ይደርሳቸዋል። በአካል ፋይል አድራጊዎች፣ ፋይል ያደረጉዋቸውን ወረቀቶች ቅጂ በወረቀት እንዲሰጣቸው ከጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) መጠየቅ ይችላሉ።

- ተከራካሪ ወገኖች ቲ.ኤ.ኤስ.አ. እና ሌሎች ከጉዳዩ ተያያዥነት ያላቸው ወረቀቶች (እንደነ በራስ መንገድ ሰነዶቹን ለተከላካይ ማድረሻ ሰነዶች)፣ በኢመይል ጭምር፣ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ይደርሳቸዋል።

<u>ከፍተኛ አደጋ መከላከያ ትዕዛዞች (ኤክስትሪም ሪስክ ፕሮቴክሽን ኦርደርስ) (ኢ.አር.ፒ.ኦ.ስ) መዝገቦች ጥያቄዎች፡</u>

- የኤክስ ፓርተ (አንድ አካል ብቻ) እና የመጨረሻ ኢ.አር.ፒ.ኦ.ስ ጥያቄዎች መደረግ ይችላሉ፣ እና በስራ ሰአታት በአካል በጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ)፣ ወይም በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ወደ DVD@dcsc.gov ኢመይል በማድረግም ፋይል መደረግ ይችላሉ። ማመልከቻው ከዲ.ሲ. ፍርድ ቤቶች ድረገጽ DC Courts website ማግኘት ይቻላል። የተመደበው ዳኛ ጉዳዩን በርቀት የፍርድ ቤት ክፍል ይሰማዋል።
- የማራዘሚያ አቤቱታ (ሞሽን ቱ ኤክስተን) ፋይል ካልተደረገ በስተቀር፣ ሁሉም ኢ.አር.ፒ.ኦ.ዎች በትእዛዙ ባለው ማብቂያ ቀን ተፈጻሚነታቸው ያበቃል።
- ክፍሉ ከኖቨምበር 9፣ 2020 ጀምሮ በከፍተኛ አደጋ መከላከያ ትዕዛዝ (ኤክስትሪም ሪስክ ፕሮቴክሽን ኦርደር) ቀጠሮ ተይዞላቸው የነበረ መዝገቦች መስማት ጀምሯል። ሁሉም ኢ.አር.ፒ.ኦ.ዎች ክርክሮችና ከኢ.አር.ፒ.ኦ.-ተዛማጅነት ያለቸው አቤቱታዎች በወረቀት ባለው ቀን ይሰማሉ። ተከራካሪ ወገኖች ከተመደበው ቀነ ቀጠሮ በፊት ምናባዊው ችሎት (ቨርቹዋል ሂሪንግ) በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ እንዴት መቀላቀል እንደሚቻል የሚያሳዩ ማስታወቂያና መመሪያዎች ያገኛሉ።
- ተከራካሪ ወገኖች የኤክስ ፓርተ (አንድ አካል ብቻ) እና ሌሎች ከመዝገብ-ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወረቀቶች በኢመይል ጨምሮ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በኩል ይደርሳቸዋል። በአካል ፋይል አድራጊዎች፣ ፋይል ያደረጉዋቸውን ወረቀቶች ቅጂ በወረቀት እንዲሰጣቸው ከጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) መጠየቅ ይችላሉ።

## <u>የቤተሰብ ፍርድ ቤት (ፋሚሊ ኮርት)</u>

ሁሉም ከአሁን በፊት እስከ ፌብርዋሪ 11፣ 2022 በአካል እንዲካሄዱ ተቀጥረው የነበሩ ችሎቶች በርቀት መካሄድ ይኖርባቸዋል። በነዚህ ችሎቶች ያሉ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳዩ ያለበት ደረጃ ችሎት (ስታተስ ሂሪንግ) ለማስያዝ ቻምበርስን ማግኘት ይኖርባቸዋል።

የቤተሰብ ፍርድ ቤት ራስ-አግዝ ማእከል (ፋሚሊ ኮርት ሰልፍ-ሄልፕ ሰንተር) ፍቺ፣ የልጅ ባለአደራነት (ቻይልድ ካስተዲ)፣ እና የልጅ ቀለብ መዝገቦች በተመለከተ መረጃና ድጋፍ ለመስጠት በአካልና በርቀት በመስራት ይገኛል። ድጋፍ የሚፈልጉ ራሳቸውን የወከሉ ተከራካሪ ወገኖች የቤተሰብ ፍርድ ቤት ራስ-አግዝ ማእከል (ፋሚሊ ኮርት ሰልፍ-ሄልፕ

ሰንተር) በ202-879-0096 ማነጋገር ወይም የሞልትርየ ፍርድ ቤት ህንጻ ክፍል ቁጥር JM-540 መጎብኘት ይችላሉ።

የሰነዶች ቅጂ ቢፈልጉ እባክዎን ወደ FamilyCourtCertifiedCopies@dcsc.gov ኢመይል ይላኩ። ሌሎች ጥያቄዎች ቢኖርብዎል የቤተሰብ ፍርድ ቤት የጥሪ ማእከልን (ፋሚሊ ኮርት ኮል ሰንተር) በ202-879-1212 ይደውሉ።

የጋብቻ ምስክር ወረቀት የተረጋገጠ ቅጂ) ሰርቲፋይድ ኮፒ ለማግኘት እባክዎን ይህን ቅጽ በኦንላይን ይሙሉ https://www.dccourts.gov/webform/marriage_certified_copy/። ሂደቱ በተመለከተ ጥያቄዎች ቢኖርብዎ እባክዎን 202-879-1212 ይደውሉ። በተጨማሪ ምስክር ወረቀቱን በአካል መጠየቅ ይችላሉ።

የፓክ (በባለአደራነት መዝገቦች የስምምነትና መተጋገዝ ፕሮግራም) አብሮ አስተዳደግ (ኮ-ፓረንቲንግ) ሴሚናሮች እንደገና በወር ሁለት ጊዜ መሰጠት ተጀምረዋል።

**<u>የግብር (ታክስ)፣ እና የኑዛዜ ማረጋገጫ (ፕሮቤት) ክፍሎች</u>**

የሞግዚትነት ቀጠሮዎች ሶስት ዓመታዊ ግምገማዎች ተጨማሪ ማስተወቂያ እስኪሰጥ ድረስ ታግደዋል።